**የዲስትሪክቱ የመሸከምያ ከረጢቶች መስፈቶች ማጠቃለያ**

**(የርዕስ 21 የዲሲ ማዘጋጃ ቤት መመርያዎች ምዕራፍ 10 (Chapter 10 of Title 21 of the DC Municipal Regulations))**

**እነዚህ መስፈርቶች፣ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ ምግብ ወይም አልኮል በሚሸጡ ድርጅቶች ለሚሸጡ ወይም ለሚሰራጩ የፕላስቲክ እና የወረቀት ከረጢቶችን ይመለከታሉ:**

- ሁሉም የሚቀርቡ **የወረቀት** እና **የፕላስቲክ** የሚጣሉ የመሸከምያ ከረጢቶች መቶ በመቶ (100%) ሪሳይክል የሚሆኑ መሆን አለባቸው።
- ሁሉም **የወረቀት** እና **የፕላስቲክ** የሚጣሉ የመሸከምያ ከረጢቶች፣ "እባክዎ ይሔን ከረጢት ሪሳይክል ያድርጉ" ወይም ተመሳሳይ ይዘታ የያዘ፣ በደንብ በግልጽ የሚነበብ፣ ሓረግ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።
  - የሪሳይክሊንግ ዓረፍተ ነገር ፊደላት በከረጢቱ ከውጪ በኩል፣ በከፊት ወይም በከኋላ ፓነል ፕሪንት መደረግ አለባቸው፤ በመገናኛ ቦታ ወይም በከረጢቱ ታችኛው ክፍል መሆን የለባቸውም።
  - የሓረጉ ፊደሎች፣ ቢያንስ ቁመታቸው የኢንች ግማሽ (0.5") ወይም ደግሞ ቢያንስ ሰባ አምስት በመቶ (75%) የከረጢቱ የፊት ፓነል  ስፋት መያዝ አለባቸው።
- የሪሳይክሉ ሓረግ ፊደል አጻጻፍ በቦልድፌስ ፎንት መሆን አለበት።
- ሁሉም የሚጣሉ **የወረቀት** የመሸከምያ ከረጢቶች ቢያንስ አርባ በመቶ (40%) ከተጠቀሙባቸው በኋላ ሪሳይክል የሚሆን ይዘታ እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።
- በፕላስቲክ የተሰሩ የሚጣሉ የመሸከምያ ከረጢቶች፣ ከፍተኛ እፍጋት ባላቸው፣ በSPI ምልክት መታወቅያ ኮድ 2 ያላቸው ፖሊተሊን ፊልም (high-density polyethylene film marked with the SPI resin identification code 2) ወይም ደግሞ ዝቅተኛ እፍጋታ ባላቸው በSPI ምልክት መታወቅያ ኮድ 4 ያላቸው ፖሊተሊን ፊልም  (low-density polyethylene film marked with the SPI resin identification code 4) የተሰሩ መሆን አለባቸው።
- ምንም እንኳን ከረጢቱ የሚበሰብስ(biodegradable) ወይም የሚቃጠል(disposable) ቢሆንም፣ ሁሉም የሚጣሉ የመሸከምያ ከረጢቶች የዚህ ክፍል መመዘኛዎች ሟሟላት መቻል አለባቸው።
- በሁለቱም፣ ማለት **በፕላስቲክ እና በወረቀት፣** የተሰራ ከረጢት፣ የወረቁቱ ክፍል የወረቀት የመሸከምያ ከረጢት መመዘኛ፣ የፕላስቲኩ ክፍል ደግሞ የፕላስቲክ የመሸከምያ ከረጢት መመዘኛ ሟሟላት አለባቸው።
- መቶ በመቶ (100%) ሪሳይክል በማይሆኑ **ፕላስቲክ** የተሰሩ የሚጣሉ የመሸከምያ ከረጢቶች በዲስትሪክቱ መሸጥ ወይም ማሰራጨት፣ በችርቻሮም ይሁን በጅምላ፣ ህገ-ወጥ ነው።
- **እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ የመሸከምያ ከረጢቶች (Reusable carryout bags)** ሆን ተብለው ለብዙ ግዜ እንዲያገለግሉ ተብለው ዲዛይን የተደረጉ እና የተመረቱ ከረጢቶች ሲሆኑ፣ ከልብስ፣ ፋይበር እና ሌሎች በማሽን ሊታጠቡ የሚችሉ ምርቶች፣ ወይም ቢያንስ ሁለት ከሩብ ሚሊሜትር (2.25 mm) ውፋሬ ያለው የሚበረክት ፕላስቲክ የተሰሩ ናቸው።